## ኣሜሪካ! ኣሜሪካ!





ፈጽሞ ሳልረሳው ኢትዮጵያዊነቴ፣
የተቀበረበት የሕፃን እትብቴ፣
እስቲ ላንጐራጉር ስለ እንጀራ እናቴ፣
ኣንዴ ላሞጋግስ ኣሜሪካነቴ...

ዓለሙን በሙሉ በምግብ ሲረዳ፣
ማንስ ግድ ብሎት፣ ማን ጥሎበት ዕዳ?
“ዘረኝነት ኣለ፣ ቀይ/ጥቁር ኣለ!”
ለሚባለው ወሬ፣ ወዴት ነው የሌለ?




የዓለም ስደተኛን ሰብስቦ፣ ኣስጠግቶ፣
ቅቤ፣ ማር ፈትፍቶ፣ ኣብልቶ፣ ኣጠጥቶ፣
በሰላም ሲያኖረን እኩል መብት ሰጥቶ፣
እንዲህ ያለ ሃገር ኣይታወቅ ታይቶ...

እስኪ ማን ኣለና እንደ ኣሜሪካ
በጥበብ፣ በዕውቀት ሞያን የሚያሳካ፣
ወደ ህዋው መጥቆ ጨረቃን የነካ፣
በሃብትም ብርታትም ኣንጀት የሚያረካ...

ኣሜሪካ ኣገሬ ኑሪልኝ ቆመሽ
ኣንድ-ኣንድ ስሕተቶችን የምጠቁምሽ
እንድትደምቂልኝ ሁሉን ኣርመሽ፣
የፍቅር ነው እንጂ፣ ኣይደል ጠልቸሽ።



? ?

የዕለትን ጥቅም ወደ ጐን ትተሽ፣
ሓሰትን፣ ሸንገላን ሰርክ ኣስወግደሽ፣
ቁሚ ለእውነቱ በሓቅ ጸንተሽ፣
እስተ ዘልዓለሙ እግዜር ይባርክሽ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።